# ብአዴንን ማፍረስ እንጅ ጠግኖ የዐማራ ጠበቃ ማድረግ አይቻልም

አንድ አንድ ግለሰቦች ብአዴንን የተወሰኑ የአመራር አባላትን በማስወግድ ጠግኖ የዐማራው ጠበቃ ድርጅት ማድረግ ይቻላል። ይሆንምአል። ብላችሁ ተስፋ የምታደርጉ የዋሆች አላችሁና እንዴት ይፍረስ ትላለህ ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል። ምክንያቴን አስረዳለሁ። መጀመሪያ ብአዴን እንዴት ተመሰረተ? ማን መሰረተው? ለድርጅቱ አባልነት የሚታጩት ወይንም የሚመለመሉት ግለሰቦች ምን አይነት ናቸው? የሚሉት ጥያቄዎች ዝርዝር መልስ ሲያገኙ ለምን መፍረስ እዳለበት ልትረዱ ትችላላሁ ። እንደሚታወቀው ብአዴን የተመሰረተው ትግራይ ውስጥ ሲሆን በምስረታው ላይ ህወሃት ወሳኝ ሚና ተጫውቷል። በመሆኑም በአመራር ላይ ያስቀመጣቸው ግለሰቦች በዘራቸው የዐማራ ደም የሌላቸው በፍልስፍናቸው የግራ ወይም የማርክሲዝም ሌኒንዝም የፖለቲካ ፍልስፍናን የተቀበሉ እና አራማጆች የሆኑ ከኢሕአፓ ተገንጥለው የወጡ ግለሰቦች ናቸው። የማርክሲዝም ሌኒንዝም ፍልስፍና ህብረተሰብ በመደብ የተከፋፈለ ነው ብሎ የሚያምን ሲሆን ይህንም ክፍፍል በሠራተኛና በከበርቴ በጨቋኝ እና ተጨቋኝ በዝባዥ እና ተበዝባዥ የተከፋፈሉ በመሆናቸው በመካከላቸው የማይታረቅ ቅራኔ አላቸው። ስለሆነም ጭቁኑ እና ተበዝባዡ መደብ ተደራጅቶ በመታገል ጨቋኙንና በዝባዡን መደብ በመደምሰስ በጨቋኙና በበዝባዡ መደብ ከርሰ መቃብር ላይ አምባገነንነቱን መመስረት ወይም ማረጋገጥ አለበት። እነዚህ መደቦች በመካከላቸው የማይታረቅ ቅራኔ ሰለአላቸው በእኩልነት አብረው ሊኖሩ አይችሉም የሚል ነው። በኢትዮጵያ በ፩፱፷ዎቹ ከተማሪዎች እንቅስቃሴ የተፈለፈሉት ፖለቲከኞች የግራ ወይንም የማርክሲዝም ሌኒንዝም ማለትም የኮሙኒዝም ፍልስፍና ተከታዮች ስለሆኑ፣ ጭቁን የሚሉት የሕብረተሰብ ክፍል ከጭቆና እና ከብዝበዛ ነፃ ለመውጣት ተደራጅቶ ጨቻኙን ወይንም የመደብ ጠላቱን መደምሰስ አማራጭ የሌለው የመደብ ግዴታው ነው ብለው ያምናሉ።

እኒህ የ፩፱፷ወቹ ፖለቲከኞች የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን የጨቁአኝ እና ተጨቁአኝ የበዝባዥ እና ተበዝባዥ መደብን ጽንሰ ሃሳብ ወደአገራችን ሁኔታ ሲተረጉሙት፤ ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦች አገር ነች።የብሔር ጭቆናም ይካሄድባታል። ስለዚህ የወያኔ መሪዎችም የዚህ የ፩፱፷ዎቹ የተማሪው እንቅስቃሴ አካል ስለነበሩ እና የግራ ፖለቲካ አራማጆች ስለሆኑ ኅብረተሠብን በጨቁአኝ ተጨቁአኝ ክፍፍል ተቀብለው፤ መደብን በብሔር በመቀየር በጨቋኙ እና በበዝባዡ መደብ ምትክ ጨቋኝና በዝባዥ ብሔር አስገቡ ። ይህም ብሔር የዐማራው ብሔር ነው ብለው በመደምደም በጨቋኙ የዐማራ ብሔር እና በጭቁኑ የትግራይ ብሔር መካከል የማይታረቅ ቅራኔ ስለአላቸው በአንድ ሃገር ውስጥ አብረው መኖር አይችሉም ከሚል ድምዳሜ ደረሱ። ስለዚህ ይህ ጨቁአኝ የዐማራ ብሔር ካልተደመሰሰ እንደ ትግራይ ያሉ ጭቁን ብሔሮች ነፃነታቸውን አያገኙም። ስለሆነም ዐማራን ደምስሰው ትግራይን ነፃ በማውጣት አዲስ የትግራይ ሬፓብሊክ ለመመስረት በሚል ወደ ትግራይ በርሃ በመግባት የትግራይን አርሶ አደርና ወጣት በፕሮፓጋንዳቸው በመቀስቀስ ለዓላማቸው አሰለፉት። በወቅቱ ኢትዮጵያን ይገዛ የነበረው ወታደራዊ መንግሥት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመዳማቱና ቅራኔ ውስጥ በመግባቱ ሕዝቡን አስተባብሮ የወያኔን በትግራይ ውስጥ የነበራቸውን እርምጃ ሊገታው አልቻለም ።ወያኔዎቹም ትግራይን ሙሉ በሙሉ እንደተቆጣጠሩ የትግራይን ሬፓብሊክ ለማወጅ እንቅፋቶች እንዳሉባቸው አስቀድመው መገንዘባቸው አልቀረም። በመሆኑም በጎንደ ክፍለ ሃገር በበለሳ አካባቢ ይንቀሳቀስ የነበረውን የኢሕአፓን ክንፍ በትነው ትራፊወቹ ተከዜን ተሻግረው ለወያኔ እጃቸውን የሰጡ ግለሰቦችን ሰብስበው አደራጇቸው። እነዚህም ግለሰቦች የግራ ፖለቲካ ፍልስፍና አራማጆች የነበሩ ሲሆን በኢትዮጵያ የብሔር ጭቆና አለ። ጨቋኙም ብሔር ዐማራ ነው ብለው በጥብቅ የሚአምኑ ግለሰቦች ናቸው።ጨቋኝ ብለው በፈረጁት የዐማራው ብሔር መደምሰስ ላይ ከወያኔ ጋር መቶ በመቶ የሚስማማ አቁዋም ያላቸው ናቸው።

ይህን እምነታቸውን እና ፀረ ዐማራነታቸውን የተገነዘበው የወያኔ አመራር የዓላማው ተጋሪ በማግኘቱ ከካድሬ ትምህርት ቤቱ አስገብቶ በማጥመቅና በማድራጀት ኢህዴን ( ኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲዊ ንቅናቄ) ብሎ

በመሰየም የራሱን አንድ ኀይል ጦር መድቦ በዋግ አካባቢ አሰፈራቸው። ምንም እንኳን የኢህዴን አመራር ተብየዎች ከአንዱ በስተቀር ሁሉም በነገዳቸው ዐማራ ባይሆኑም ከአብዛኛው የወያኔ ወታደር በተሻለ ዐማርኛን መናገር ብቻ ሳይሆን እንደናታቸው ቋንቋ አቀላጥፈው ስለሚያውቁ ወያኔ የዐማራውን ምድር አቋርጣ አዲስ አበባ መድረስ እንድትችል የዐማርኛ ተናጋሪ ክንፍ በመሆን ከፍተኛ አገልግሎት አበርክተዋል። ወያኔዎችም ወታደራዊዉን መንግሥት አስወግደዉ መላዋን ኢትዮጵያን በቁጥጥራቸዉ ስር ካደረጉ እና የሽግግር ጊዜአቸውን አጠናቀው ወደ ቋሚ መንግሥትነት ተሸጋግረናል ብለው በወሰኑበት ጊዜ ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦች ስብስብ እንጂ አንድ አገር አይደለችም የሚል ሕገመንግሥ አጽድቀው ወደቋሚ መንግሥነትነት ተሸጋገርን ሲሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢሕዴን) ብለው ትግራይ ውስጥ ያደራጁትን ሕብረ ብሔራዊ ድርጅት ብሔረ ዐማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) ብለው በመሰየም የወያኔ መሳሪያ ሁኖ ዐማራውን በማዳከም ብሎም የማጥፋት ዘመቻቸው ግንባር ቀደም ተጫዋች እንዲሆን ተልኮ ተሰጠው።ከላይ እንዳልሁት የዚህ ድርጅት አመራሮች በፀረ ዐማራ አቋአማቸው ከወያኔ ጋር ስለሚስማሙ፣ ከሕብረ ብሔር ድርጅትነት ወደ አንድ ብሔር ድርጅትነት ብሔረ ዐማራ ድርጅትነት ውረዱና ዐማራን በማጥፋት ዘመቻ እንዲ ተባበሩ ተልእኮ ሲሰጣቸው ይህን ተልእኮአቸውን ሳያወላውሉና ጊዜ ሳያጠፉ ወዲያውኑ ተቀብለው መተግበር ጀመሩ። እስተ አሁን ድረስም  እየተገበሩት ነው። ብአዴን ህልውናው እስታለ ድረስ የወያኔ አገልጋይነቱን እንደሚቀጥልበት የሚጠራጠር ኢትዮጵያዊ በተለይም ዐማራ ካለ ሲበዛ የዋህ መሆን አለበት።በአሁኑ ጊዜ የወያኔዎች የረዥም ጊዜ ዓላማ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ግልጽና ግልጽ ነው። ኢትዮጵያን አጥፍቶ አዲሲቱአን እና ታላቋዋን የትግራይ ሬፓብሊክ መመሥረት ነው። የህን ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ ያሰናክለናል ብለው የሚያስቡት የዐማራውን ነገድ ስለሆነ፤ ይህን ማህበረሰብ ከቻሉ ከምድረ ገጽ ማጥፋት፣ ያ የማይሆን ከሆነ ደግሞ ዓላማቸውን ማደናቀፍ በማይችልበት ደረጃ ማዳከም። ስለዚህ ለተልኮአቸው እንደመሳሪያ ለሚጠቀሙበት ድርጅት ለብአዴን አባልነት የሚመለመሉት ግለሰቦች በደንብ ተጠንተው ይመለመላሉ፤ እድገትም የሚሰጣቸው የወያኔን የረዥም ጊዜ ግብ ለመተግበር የማያወላውሉ መሆናቸውን ሲያስመሰክሩ ብቻ ነው። ለምሳሌ ታምራት ላይኔ የተባለውን ግለሰብ የቀድሞው የኢሕዴን በሁዋላም በአዴንን ይመራ የነበረ ብንወስድ፤ ምንም ያህል ጊዜ አልወሰደበትም የተሰጠውን ትእዛዝ ሲፈጽም። ብፁ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትሪያሪክን ከመንበራቸው ሲያባርር። የመከላከያ ሚኒስተር ሆኖ ሱማሌ ክልል ህዶ ይህን ትምክህተኛ ማንነትህን አሳየው ያለውን ንግግር ዐማራው ይቅርና በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምን የምታምን ግለሰብ አይረሳውም።

ይህ ግለሰብ አምኘበታለሁ ብሎ ይዞት የነበረውን አቋአም ቀይሮ ሲገለባበጥ ሞራሉን የማይጎረብጠው እንደሱ አላየሁም። መጀመሪያ በኮሙኒስት ዓለማቀፋዊነት ተጠምቄአለሁ ብሎ ኢሕአፓን ተቀላቀለ። ይህን ዓላማውን በመክዳት ለጠባብ ብሔርተኛ ድርጅት እጁን ሰጠ። ከዚያም የአንድ ብሔር ድርጅት መሪ ሁን ሲሉት ሳያቅማማና ሞራሉን ሳይቆነጥጠው የጌቶቹን ትእዛዝ ተቀብሎ ፈጸም። ከዚያም አሳዳሪዎቹ አገልግሎቱን እንደጨረሰ ሲረዱ እራሱን የሚከስ ጽሁፍ ጽፈው በብሔራዊ ቴሌቪዥን ካሜራ ፊት ቀርበህ አንብብ ሲሉት እጁና ክንፈሩ እየተንቀጠቀጠ ወንጀለኛ መሆኑን በአደበበይ በራሱላይ መሰከረ። በመሆኑም ጌቶቹ ወያኔዎች ዘብጥያ አወረዱት። ከወያኔ ዘብጥያ ውስጥ ጌታን አገኘሁት በማለት ኮሞሙኒስትነቱን አውልቆ ጥሎ በየመድርኩ በመተወን ኩባያ የሚሞላ እንባ እያነባ ተከታዮቹን ያስለቅሳል። በጠቅላይ ሚኒስተርነት እና በመከላከያ ሚኒስተርነት የመራው አገር ሕዝብ ከአምሳ በመቶ በላይ ተከታይ ያለውን ሃይማኖት መሳለቂያ ማድረግ የሰውየውን የሞራል ድህነቱን ቁልጭ አርጎ ያሳያል።

ታምራት ወያኔ በብአዴን ውስጥ ካሰባሰባቸው ግለሰቦች አንዱ ሲሆን የቀሪዎቹን ግለሰቦች ስብጥር በቡድን በቡድን በመከፋፈል ምን እንደ ሚመስል እንመልከት።በአንደኛው ቡድን ውስጥ የተሰባሰቡት ግለሰቦች በነገዳቸ ዐማራ ያልሆኑ እና ትግል ሀ ብለው ሲጀምሩ የግራ ወይም የኮምኒስት ፍልስፍና ተከታዮች

ከመሆናቸውም በተጨማሪ ዐማራው ጨቋኝና ተጠቃሚ ብሔር ነው ብለው የሚያምኑና በዐማራው ሕብረተሰብ ላይ ጥላቻ ያላቸው ናቸው። በመሆኑም "ጭቁን ብሔሮች" ይህን ጨቋኝ ብሔር ካልደመሰሱ የብሔር መብታቸው አይከበርም ብለው የሚታገሉ እና እስከመጨረሻ እስትንፋሳቸው ህወሃትን ለማገልገል ወስነው ከወያኔ ጋር የተቅላቀሉ ናቸው ። እነዚህ ግለሰቦች በዐማራው ነገድ ላይ ባላቸው ገደብ የለሽ ጥላቻ እና ስልጣን አማካኝነት ባሁኑ ጊዜ የዐማራውን ገበሬ አርሶ ያመረተውን ምርት በተለያየ ስበብና ምክንያ በመዝረፍ መሬቱን በመንጠቅ የከበሩ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በዐማራው ላይ ብዙ ወንጀል ፈጽመዋል እየፈጸሙም ነው። ለወደፊቱም ዐማራው ተደራጅቶ እጃቸውን ይዞ ካላስቆማቸው በስተቀር ዐማራን በማጥፋት ተልኮአቸው ይቀጥላሉ እንጅ የዐማራው ጠበቃ አይሆኑም። እነዚህን ሲጀምር በነገዳቸው ዐማራ ያልሆኑ እና ዐማራው ጨቻኝና በዝባዥ ብሔር ነው በመሆኑም ይህ ጨቋኝ ብሔር እስካልተደመሰሰ ድረስ የተጨቆነችው የትግራይ ብሔር ነፃነት አይረጋገጥም ብለው የሚያምኑ ስለሆነ፤ ልባቸው ተለውጦ ለዐማራው ጥብቅና ቆመው መብቱን ያስጠብቁለታል ብሎ ማሰብ ከእባብ እንቁላል እርግብ ትፈለፈላለች ብሎ መጠበቅ ነው። ይህ ቡድን በጠቅላላ ዐማራው ጠላታችን ነው ብሎ ያምናል። ጠላት ደግሞ ለጠላቱ ኀልውና ይቆማል ተብሎ አይጠበቅም። ጠላት ለጠላቱ ኀልውናና ጥቅም ይቆማል ብሎ የሚጠብቅ ግለሰብም ሆነ ሕዝብ ሃለ ችግሩ ጠላቴ ለጥቅሜ ይቆምልኛል ብሎ የሚጠብቀው አካል እንጅ የሌላው አይደለም።

ሁለተኛው ቡድን በዐማራው አካባቢ ተወልደው ያደጉ በነገዳቸው ትግሬ የሆኑ እና ግማሽ ትግሬ ሆነው ግማሻቸው ዐማራ፣ አገው፣ ቅማንት፣ ወዘተ ነገዶች የተወለዱ ናቸው። ይህም ቡድን እንደላይኛው ሁሉ በሙሉ ወይም በግማሽ ትግሬነታቸውን የሚያስቀድሙ በመሆናቸው፤ የዐማራ መድከም ብሎም መጥፋት ምንም የማይሰማቸው ስለሆኑ ለወያኔ ዓላማ ፍጻሜ መድረስ ሌት ተቀን የሚተጋ በመሆኑ የልቦና ለውጥ አድርጎ ለዐማራው ኀልውናና መብት ሊቆም ይችላል ብሎ ማሰብ ከየዋህነት ያለፈ ሞኝነት ነው። ይህኛውም ቡድን እንደ ላይኛው ቡድን የወያኔን ዓላማ ለማስፈጸም በታማኝነት ስለሚያገለግል ወያኔ ዐማራን በማዳከም ብሎም በማጥፋት አጀንዳው እንደ ቀኝ እጁ የሚያየውና የሚያምነው ነው።

ሦስተኛው ቡድን ወያኔዎች የዐማራ ክልል ብለው በከለሉት ውስጥ ከሚኖሩት አናሳ ነገዶች መካከል ለዐማራው ጥላቻ ያላቸውን ግለሰቦች ያሰባሰቡበት ቡድን ነው። ይህም ቡድን በወያኔ ፀረ ዐማራ ፕሮፓጋንዳ ዕዕምሮው የተበከለ ስለሆነ እንደላይኞቹ ሁለት ቡድኖች ወያኔዎች የሚያዙትን ትዕዛዝ እንደወረደ የሚያስፈጽም ቡድን ነው። ስለሆነም ይህን ስብስብ ወደ ዐዕምሮው ተመልሶ የዐማራው አጋር ይሆናል ብሎ በተስፋ መጠበቅ ስህተቱ የተስፋ አድራጊው እንጅ የዚህ ፀረ ዐማራ ስብስብ አይደለም።

አራተኛው ቡድን ከዐማራው ነገድ የተወለዱ ግለሰቦች የተሰባሰቡበት ቡድን ሲሆን ይህን ቡደን የወያኔ ቀኝ እጅ የሆኑት የላይኞቹ ቡድን አባላት በጥንቃቄና በጥናት መልምለው ወደ ድርጅቱ ያስገቡአቸው ግለሰቦች ስብስብ ነው። የዚህ ቡድን አባላት የተላያየ ድክመት የተጠናወታቸው ግለሰቦችን ያካተተ ስብስብ ነው። የዝሙትና የመጠጥ ሱስ የንዋ ፍቅር እንዲሁም በተፈጥሮአቸው የባንዳነት ጠባይ ባላቸው ግለሰቦች የተሞላ ነው። ይህ ቡድን ስልጣንን በሚመለከት ለይስሙላ ከወንበር የተቀመጠ ሲሆን እውነተኛው ስልጣን ከላይ በተጠቀሱት የወያኔ ወኪሎች እጅ ስለሆነ ይህ ቡድን ለነዚህ የወያኔ ወኪሎች ታዛዥ ነው። ስለዚህ ይህን ቡድን በዝቅተኛ የስልጣን እርከን ላይ ያለ ከመሆኑም በላይ ተመልምሎ ወንበር ከማግኘቱ በፊት ጀርባው ተጠንቶ፤ በተለያየ ድክመት ወይም ሱስ የተጠመደ በመሆኑ የተመለመለ ሲሆን፣ ሱሱን ለማርካት የጨበጣትን ስልጣን በመጠቀም የአባትህ ቤት ሲወረር አብረህ ውረር በሚል የተበላሸ ፍልስፍና እንደ ላይኞቹ ቡድን ሁሉ በሙስና የነቀዘ እና የተበላሸ ከመሆኑም በተጨማሪ የባንዳነት ጸባይ ስላለው የናትህን ሆድ ቅደድ ብለው ቢያዙት ትዕዛዛቸውን ለመፈጸም የማያወላውል ስለሆን ለዐማራው ሊቆም ችሎታም ሆነ ወኔ የለውም አይጠበቅበትምም።

በመጨረሻም በተለያየ ጊዜና ምክንያት ብአዴንን የተቀላቀሉ ከነዚህ ቡድኖች ውጭ የሆኑ በጣም በዝቅተኛ የስልጣን እርከን ላይ ማለትም በወረዳ ደረጃ ያሉ የዐማራ ልጆች አሉ። እነዚህ የዐማራ ልጆች እንደሁላችን ቆሽታቸው እያረረ እየተቃጠሉና ግፉ እያንገፈገፋቸው ጊዜና ሁኔታን የሚጠብቁ ናቸው። ይህ የመጨረሻው ቡድን መሪ ሁኖ ብአዴንን ከወያኔ መዳፍ ለማላቀቅእና አመራሩን ከመጀመሪያዎቹ ሁለት ቡድኖች ነጥቆ ለመረከብ አቅሙም ሆነ ችሎታው የለውም። ይሁን እንጅ በህቡዕ ለተደራጀ የዐማራ ኅልውና አስጠባቂ ድርጅት ይህ የመጨረሻው ቡድን የማይናቅ አስተዋፆ ሊያበረክት ይችላል። በውስጥ አርበኝነት መረጃ በማቀበል በህቡዕው ከተማውን ከገጠር የሚያገናኝ መስመር ዘርግቶ ለትግሉ የሚያስፈልጉ ገጠር የማይገኙ ቁሳቁሶችን በማቀበል ቁልፍ ሚና ሊጫወት ይችላል። ከላይ በተራ ቁጥሮች የተዘረዘሩት የወያኔ ሥራ አስፈጻሚዎች በዐማራው ላይ የፈጸሙትንና የሚፈጽሙትን ወንጀል ማስረጃ በመሰብሰብና ሰውሮ በማስቀመጥ ድርሻውን ሊወጣ ይችላል።

የመጀመሪያው ቡድን አባላት የታወቁ ቢሆኑም እንዲሁ ለማስታወስ ያህል በረከት አዲሱ ለገሰ ህላዌ ወዘተ። በሁለተኛው ቡድን ከሚገኙት እነካሳ ተክለ ብርሃን እነ ዓለምነው መኮነን ወዘተ። በሦስተኛው ቡድን ውስጥ ደግሞ እንደነ ደመቀ መኮነን ያሉት ሲሆን ብአራተኛው ቡድን የሚካተቱት ደግሞ እንደነ ገነት ዘውዴ ዳዊት ዮሐንስ ገዱ አንዳርጋቸው የመሳሰሉት የወያኔ አሳዳሪዎቻቸው ሲነቀፉባቸው እንደ ህፃን ልጅ ስቅስቅ ብለው የሚለያቅሱ። ምሳሌ ገነት ዘውዴ መለስ ዜናዊ በዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ ተነቀፈ ብላ እንደነፈረቀችው ማለት ነው:: አሳዳሪወቻቸው ኢትዮጵያን እንዴት እንደሚያፈርሱ ከውጭ አገር ሰላይ ጋር ሲዶልቱ ሻይ አፍልተው ለዶላቾቹ ለወያኔ ጌታውና ለውጩ ሰላይ አቅርበው ምስጢራቸውን አውርተው እስቲጨርሱ ውጭ ወጥቶ እንደውሻ ከበሩ አካባቢ ኩርትም ብሎ ተቀምጦ የሚጠብቅ። ምሳሌ ዳዊት ዮሐንስ ለሲአይኤው ፖል ሄንዚ እና የወያኔው ብርሃኔ ገብረ ክርስቶስ በኢትዮጵያ ላይ ሲዶልቱ ሻይ አቅርቦላቸው እንደወጣውና እንደጠበቃቸው ማለት ነው። እንደ ገዱ አንዳርጋቸው ያለው ደግሞ ለአድርባይነቱ ወሰን የሌለው ግለሰብ በኢትዮጵያ መንግሥት ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ትግራይ የተከዜን ወንዝ ተሻግራ በፍየል ግንባር ልክ የምሆን መሬት ኑሮአት እንደማያውቅ ታሪክ እያስረዳ፤ ጎንደር ከተማ ሊጠጋ ምንም ያልቀረው የግጨውን አካባቢ ለም መሬት ለትግራዩ ለአባይ ወልዱ አስረክቦ ምንም ሳያፍር የትግራይንና የዐማራን ክልል የደንበር ችግር ፈታሁ ለዐማራውም ክልል ያልተጠበቀ መሬት አስገኘሁለት ደስታችሁ ይብዛ የሚሉ አይነቶች በሀፍረታቸው የሚያጌጡ ባንዳዎች ናቸው። አፍረት ይሉኝታ የሚባሉት ትልቅ የሰው ልጆች እና በተለይም የኢትዮጵያውያን እሴት የሌላቸው ግለሰቦች ገዱና መሰሎቹ ናቸው። ይህ ገዱ የሚባል ግለሰብ ሃፍረት የሚባል ነገር ቢኖረውማ ተጨማሪ መሬት ለአባይ ወልዱ አስረክቦ የዐማራ ሕዝብ ደስ ይበልህ ተደራድሬ ያልታሰበ ተጨማሪ መሬት አመጣሁልህ ብሎ አባይ ወልዱን ማቀፍ ይቅርና ከአባይ ወልዱ ጋር ጎን ለጎን መቀመጥ በቀፈፈው ነበር። አባይ ወንጀለኛ ስለሆነ ከኢህአዴግ ተባሮ እስር ቤት ገብቶ ካላየሁት ኢህአዴግ ከሚባለው ድርጅት የለሁበትም ብሎ ስንብት በጠየቀ ነበር። ምክንያቱም የዐማራ ክልል ብለው ከከለሉትና ገዱ በአስተዳዳሪነት ከተሰየመበት የዐማራ ዕምብርት እና ለሦስት መቶ ዓመታት የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ከነበረቸው ጎንደር ውስጥ የሚኖሩ የዐማራ ልጆችን አባይ ወልዱ መቀሌ ሁኖ በላከው አፋኝ ቡድን የተፈጸመው ወንጀል በከነከነው ነበር። ውድ የዐማራ ልጆችን አሳፍኖ ወስዶ እስከ አሁን ድርስ በወያኔ ማጎሪያና ማሰቃያ ክፍል እየተሰቃዩ ይገኛሉ። እድሜ ለጀግናው ወንድማችን ለደመቀ ዘውዱ የተወሰኑትን የአባይን አፋኞች ሲከላከል በወሰደው የአጸፋ እርምጃ ለአባይ የማይረሳ ትምህርት በመስጠቱ በአሁኑ ጊዜ ወያኔን ይይዘው ይጨብጠው ያሳጣውን የዐማራ ተጋድሎ ቢያቀጣጥልም፣ ገዱ የሠራው የባንዳነት ሥራ የሚያቅለሸልሽ ነው። ከላይ ከቡድን አንድ ጀምሮ እስከ ቡድን አራት በተዘረዘሩት ግለሰቦች እግር ከወርች ተጠፍሮ በፀረ ዐማራነት የታነጸን የወያኔ ሥራ አስፈጻሚ የአሆነን ድርጅት ጠግኖ የዐማራው ሕዝብ ተቆርቋሪ ማድረግ አይቻልም። ስለዚህ ዐማራውን እና ኢትዮጵያን ከወያኔ የሲኦል ኑሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ ነፃ ለማውጣት ከተፈለገ በአዴንን ማፍረስ ቀዳሚው ተግባር መሆን አለበት።

በሶሻል መገናኛ እንደተረዳነው በአሁኑ ጊዜ የሱዳን ወታደሮች በወያኔ ጋባዥነት የኢትዮጵያን ድንበር ጥሰው በወያኔ የዐማራ ክልል የተባለውን ወረውታል። የዐማራ ህጻናትን ምንም ሳያጠፉ እየለቀመ ለወያኔ አሳልፎ በመስጠት ግብረ ሰዶል (ቶርቸር) እንዲፈጸምባቸው የሚተጋው የወያኔ አገልጋይ ብአዴን ድንበራችን ሲጣስና እርስታችን ሲወረር አንድ ቃል ትንፍስ አላለም።

እናም ይህን ብአዴን የተባለ የባንዳና ከሃዲ ብሎም ፀረ ዐማራ ጥርቅም በውስጥም በውጭም ያለን ዐማራዎች እና ማንኛውም አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ተረባርበን ማፍረስ ግዴታችን መሆን አለበት። ብአዴንን ማፍረስ ማለት የወያኔን ትልቅ መሳሪያ መንጠቅ ማለት ነው። መሳሪያውን የተነጠቀ ጠላት ደግሞ ለማጥቃት በጣም ቀላል ነው። የወያኔ አገልጋይ እና የባንዳ ጥርቅም የሆነው ብአዴን እንደድርጅት ህልውናው እስተቀጠል ድረስ ወያኔን የማስወገድ ትግሉ የተራዘም ይሆናል።

ብአዴንን ለማፍረስ ጥርት ያለና ወሳኝ የሆነ ወዳጅ እና ጠላቱን አብጠርጥሮ የለየ ጠንካራ የዐማራ ድርጅት ያስፈልጋል። ለዚህም በዐማራው ተጋድሎ የተጀመረውን እንቅስቃሴ እና አስኩአል ድርጅቶች ማጠናከር የግድ እና አሁኑኑ መረባርብ ከሁሉ በፊት ቅድሚያ የሚሰጠው የቤት ሥራችን መሆን አለበት። የዐማራ ድርጅቶች አስኩአል የሆኑት በአንድነት ከተሰባሰቡና አንድ ጠንካራ ውህድ ድርጅት ከሆኑ ትግሉን በከተማም በገጠርም በማጡአጡአፍ በመጀመሪያ በቡድን አንድ የተጠቀሱትን የወያኔ አገልጋይ የዐማራ ጠላት ግለሰቦች ማስወገድ ይቻላል። ይህ በመጀመሪያ እረድፍ የተሰለፈው ፀረ ዐማራ የወያኔ ሎሌ ቡድን ከተወገደ የወያኔ ዐማራውን የሚመለከትበት ዐይን ይጠፋል። የመጀመሪያው ቡድን ከተወገደ ሁለተኛው ቡድን ዐይኑ የጠፋ ብቻ ሳይሆን አእምሮውም የደነዘ ስለሚሆን ይህን ቡድን ለማስወገድ ይቀላል። ይህ ሁለተኛው ቡድን ከተወገደ ብአደን በተግባር ይፈርሳል። ስለሆነም እነዚህ ሁለት ቡድኖች ሲወገዱ ወያኔ በዐማራው ላይ የዘረጋው የቁጥጥርና የጭቆና መረብ ያከትማል። በተፋጠነ ሁኔታ የወያኔ እድሜ ሊያጥርና የዐማራው ሰቆቃ ሊያከትምና ነፃነቱን ሊቀዳጅ የሚችለው በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቡድኖች የተሰባሰቡትን የወያኔ መሳሪያዎችን ማስወገድ ሲችል ነው።

ዐማራው በጠላቱላይ ድል ይቀዳጃል!

ኢትዮጵያ ለዘልዓለም ትኖራለች!